# አጥፊዉና ዉሸታሙን በሕብረት እናስወግድ ለአገራችን አይበጁትም

(ከአሸብር)

በዚች የምንኖርባት አለም ላይ አጋርነትንና እዉነት ይዞ የሚጓዝ ማንኛዉም ፍጡር የተነሳበትን አላማ ግቡ ላይ ለማድረስ ብዙ አይነት ዉስብስብና አመኬላዎች በየአቅጣጫዉ ስለሚፈታተኑት ሃቀኝነቱን ለሁሉም ዜጋ ለማሳመን የሚፈጅበት ግዜ በቀላሉ የሚገመት ጉዳይ አይደለም። አይጥ ከተራባበት የመኖርያ ቤት በቀላሉ ከነዚህ ተባይ መንጋ ነጻ መሆን አይቻልም:: ጨርሶ ለማጥፋት ቢታሰብም የመሸጉበት ቤት ጠቅልሎ ይዉደም ቢባል ደግሞ መጠግያ አልባ በረሃ ላይ ቆሞ መቅረትን ያስከትላል። ከተደበቁበት ጉድጓድ አንድ ባንድ እናጥፋ ቢባል ቦታቸዉን እየቀያየሩ አንድ እንኳ ሳትገድል ቁመህ መቅረት ይሆናል:: እነ ብልጣ ብልጦቹ እንደሆነ በቀላሉ የሚወገዱ አይደሉም:: ተንኮለኛና መዉጫ ቀዳዳ የሚያዉቅ በቀላሉ ማጥፋት አይቻልም:: ተበዳዮችም ከበደል ሁሉ መላቀቅ የማይችሉት ዋናዉ ምክንያት ተባብረዉ ተባዮች የሚዝናኑበትን መዉጫ ቀዳዳ ጉድጓድ በመድፈን በአጭሩ እንዲቀጩ ካልተደረገ በቀር አበሳችን እየከፋ እንጅ እየቀለለ መሄድ አይችልም:: አስፈላጊ ባልሆኑ ጉዳዮች እርስ በራሳችን ከመነታረክ ይልቅ ተባብረን አገራችን ከተባዮች መንጋ ማንፃት አንዱና አብዩ መፍትሄ ነዉ። ነገር ግን አይጥን እያደነ የሚካላከልልንን አያ ድመትን እየወቀስን መኖሩ በቤታችን አካባቢ ለተንሣበበብን ችግር መፍትሄ ሊሆነን አይችልም። ሕጻን ሁኜ ያደረኩት በደል እስከአሁን ድረስ ከጭንቅላቴ ሊፋቅልኝ አልቻለም። በተኛሁና በተነሳሁ ቁጥር ድርጊቱ ስዕላዊ ሆኖ ከፊቴ እየተደቀነብኝ የመንፈስ እረፍት እንዳጣ አድርጎኛል።

**<u>በደሉ እንዲህ ነበር</u>። በወላጆቻችን ትእዛዝ መሰረት እኔና ታላቅ ወንድሜ ላሞቻችን አዉሬም እንዳይደፍራቸዉና የአርሶ አደሩን እሕልም እንዳይበሉ ጠንክረን እንድንጠብቅ አደራነት ተሰጥቶን ስንጠብቅ ከወጣነበት ስአት ጀምሮ ወደ ቤት እስክንመለስ ድረስ ቀኑን በሙሉ ሳያርፍ ወንድሜ ብቻዉን ነበር የሚጠብቀዉ:: እኔ ግን አመመኝ ቆረጠኝ እያልኩኝ ምክንይት በመደርደር ከአንድ ጥላ ስር ቁጭ ብየ ሳንቀላፋ እዉልና እቤት ስንገባ ሽሉክ ብየ አባቴ ከተቀመጡበት ቦታ ቀድሜ በመገኘት ቀኑን ሙሉ እኔ ብቻ ስጠብቅ እንደዋልኩ አድርጌ የዉሸት ዜና ስነግራቸዉ በቁጣ ወንድሜን ይጠሩና ግርፋቱናና ስድቡን አግኝቶ የተዘጋጀልን እራት በንዴት አልበላም ብሎ ለእኔ ይተዉልኝና ሙጥጥ አድርጌ እበላዉ አለሁ። እንግዲሕ እግዚአብሄር ያሳያችሁ ገመና ከታች ወንድሜን ለሰራዉ ደግ ስራ ምስጋና ሲገባዉ እሳት ላይ እንዲጠበስ ክርቢትና እንጨት ያቀበልኩት እኔዉ ዉሸታም፤ ቀጣፊ ወንድሙ ነኝ። ነገር ግን እዉነት**

እንደተደበቀች አትቀርምና አንድ ቀን ዉድ አባታችን ላሞች ወደ ምንገታበት ሜዳ መጣሁኝ የሚል ማስጠንቀቅያ ሳይሰጡን ይመጡና ትልቅ ወንድሜ ብዛት ያለዉን ከብት ለማገት ከአንዱ ጠርዝ ወደሌላዉ ጠርዝ እየተሯሯጠ ብቻዉን ሲደክም አዩትና ወንድምሕ የት ሂዶ ነዉ ብቻህን የምትደክመዉ ይሉታል? ወንድሜ የአባታችን ጭካኔ የሞላበት ቅጣት በእኔ ዉሽታም ወንድሙ ሰበብ ስለቀመሳት እኔን ላለማስገረፍ ምክንያት ደረደረላቸዉ:: የራስ በሽታ ስላስቸገረዉ አረፍ በል ተኛ ብዬዉ ከጥላዉ ስር ተኝቷል ሲላቸዉ አባቴም ከተኛሁበት መጡና ወይ ልጄ በል ተነስ እንዴት ሲያምሕ ወደቤትሕ አትመጣም ነበር እያሉ ሲናገሩ ከእንቅልፍ ሠመመን ባነንኩና ሳላስበዉ እዉነቱን መለፍለፍ ጀመርኩኝ:: ኧረ እኔ አልታመምኩኝም ሁል ግዜ ነዉ የምተኛዉ ወንድሜ ብቻዉ ነዉ ሲጠብቅ የሚዉለዉ ብዬ የተደበቀዉን ሁሉ ዘላበድኩላቸዉ:: አባታችንም አንተ አህያ ባለፈዉ ቀን ምን ብለህ ነገርከኝ ያንተን የዉሸት ቃል ሰምቼ ልጄን ያሰቃየሁት ይሉና መፈጠሬ እስከምጠላ ገርፈዉ ለወደፊቱ እንዲሕ ያለ ዉሸት ላለመድገም ቃል ገብቼ ቅጣቱ አከተመልኝ። እኔ ስገረፍ ወንድሜ በሩቅ ሆኖ ያለቅስ ነበርና አባቴ ና ብለዉ እሱ ስለተመታ አንተ ምን አስለቀሰሕ ሲሉት ወንድሜ እኮ ነዉ ይላቸዋል:: ባለፈዉ ግዜ አንተ ስትገረፍ እሱ ደንታ አልሰጠዉም ሲሉት ሕጻን ስለሆነ ነዉ ልብ ሲያደርግ ኋላ ይቆረቁረዋላ ይላቸዋል:: ያ ደጉ ወንድሜም የእድሜ ባለጸጋ አልሆነም:: በበሽታ ምክንያት ከዚሕ አለም በሞት ሲለየኝ ሀዘኔ ድርብ ድርብርብ ሆነብኝ:: ይሕች አለም የዋሾዎች አለም ለመሆኗም ከራሴዉ የሂወት ታሪክ መረዳት ችየ አለሁ:: እዉነትም ትመነምናለች እንጅ እንደማትጠፋ ተገነዘብኩኝ። እንግዲሕ ዉሸትን ተንተርሰዉ የሚያናፍሱ ምላሶች አንድ ቀን በህዝቡ አመጽ ይለጎማሉ ለሃቅ የተነሳዉም በአሸናፊነት ይወጣል።

ወደ ተነሳሁበት አርእስት ልመለስና ትንሽ ልበል:: በአገሩ ላይ ፍትሕና ነጻነት እንዲኖር በቆራጥነትና በሀቀኝነት ሲታገል የኖረዉ ግለሰብም ሰዉ ነውና አርጅቶ ይሞታል:: ከመሞቱ በፊት ግን ከወላጆቹ የቀሰመዉ ታሪክና የአገር ፍቅር ለተተኪዉ ትዉልድ ካላስተላለፈ በቀር ታሪክም እንደሰዉ አርጅቶ ይሞታል። ቀንደኛ የኢትዮጵያ ጠላቶች ወያኔዎች አኩሪዉ ባሕላችንና ለዘመናት ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እየተላለፈ የኖረዉን ታሪካችን አጥፍተዉ አሁን በምናየዉ አሳዛኝና የሻገተ የአስራ ስምንት አመት የዉርዴት ታሪክ ሕዝባችን በሃይል እንዲቀበለዉ እያስገደዱ የቤት ስራቸዉ እየሰሩ ነዉ:: እኛም እንደ አበደ ዉሻ በየጎዳናዉ ከመጮሕ በቀር ይህ ነዉ የሚባል ጠቃሚ ዉጤት ልናመጣ አልቻልንም:: ይባስ ብሎ እርስ በርሳችን በምናደርገዉ መራቆት በይበልጥ ወያኔዎች ጡንቻቸዉ እንዲዳብር ረድቷቸዋል። የታሪክ ባለቤት የሆነዉን ተቆርቋሪዉ ወገን እያደኑ ለዘመናት ይዞት የቆየዉን ክብረ ወሰን በመግፈፍ በማያምንበት በክልልና በዘር ከፋፍለዉ አገሪቱ የዋሾዎች መናሃርያ አድርገዋታል። ወያኔዎች ከምስረታቸዉ ጀምረዉ የተነሱበት ዋና አላማ የነበረዉን አጥፍተዉ አዲስ የራሳቸዉን ዘግናኝ የአረመኔዎች የሕጻናት ገዳይ ታሪክ በነ አሉላ አባነጋና ዘርዐይ ድረስ ለመተካት

ነዉ። ይህ አይነቱ እቅድ ለመልካም አርአያነት ለሰዉ ልጅ ክብርና መብት ተጠቅመዉበት ቢሆን ኑሮ ማን እንደ እነሱ ታዋቂና አዲስ ምእራፍ ከፋች ይሆን ነበር? ወራዳና ክብርን ለመነናጸፍ ያልታደለ ሁሉ የስራዉ ዉጤት ለዕኩይነት ተግባር እንጅ ለመልካም አርአያነት ሊዉል አይችልም። ወያኔዎች ታቴ ብለዉ መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማንነታቸዉ ሲያስተዋዉቁት የተናገሩት ቃል ቢኖር ልንበታትናችሁና ልናጠፋችሁ እየመጣን ነዉ ሲሉ ማንም ከቁምነገር የቆጠረዉ አልነበረም - ያለ ኢሕአፓ በቀር:: ኢህአፓም ወያኔዎች አገራችንን ለማጥፋትና ይዘዉት የተነሱ አላማ ኢትዮጵያን ለመሸንሸን መሆኑ ነጋ ጠባ ሕዝቡ እንዲያዉቅ በተለያየ መንገድ አሳዉቋል:: ታግሎ ብዙ መስዋእትነት ከፍሏል:: ነገር ግን ሰሚ አላገኘም:: ይልቁን እንዲህ ብሎ መጭዉን የኢትዮጵያ እጣ ምን ሊመስል እንደሚችል በመናገሩ አንተ ነብይ ያለህ ማን ነዉ በማለት አሁን የለዉጥ ሃዋርያዎች ነን እያሉ የሚመጻደቁት ዶክተርና ፕሮፌሰር ባዮች ከፋሽሽቶችና ጠባቦች ጋር ክንዳቸዉ በማጣመር የማጥፍት ዘመቻ አዉጀዉበት ስንቱን ሃቀኛና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን አሳጥተዉታል። ኢሕአፓ መንትያ ምላስ እንደ ወያኔዎች ይዞ ቢነሳ ኑሮ የስልጣን ባለቤትነቱ ማንም ሊነጥቀዉ አይችልም ነበር:: ነገር ግን በደርግ ምትክ ኢሕአፓ ተተካ መባሉ ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም እንደተባለዉ አባባል ኢሕአፓም በአገራችን ስርነቀል ለዉጥ መምጣት አለበት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ አድሎ የለለበት ሥርአት ተመስርቶለት መብቱና ግዴታዉ አዉቆ የፈለገዉን ሊሾምና ሊሽር የሚችልበት ሕገ ደንብ ደንግጎ ለህግ ተገዥ የሚሆን መሪ ማምጣት የሚቻለዉ ሕዝቡን በቅድምያ በማደራጀትና በማስተማር ብሎ በማመኑ ነዉ ስልጣን ሊይዝ ያልቻለዉ:: ሌላ ምንም አይነት ምክንያት አልነበረም:: የሕዝቡ ድጋፍም ሆነ እዉቀቱ በእጁ ነበረ:: ኢሕአፓ ተሳስቷል የምለዉ ለዘመናት በባላባታዊዉ ሥርአት የላሸቀች አገራችን፣ በነብሰ በላ ፋሽሽት የቁም ስቃይ ያየች፣ በባእዳን ጠላቶቻችን እየተደገፉ ሊገነጣጥሏት ከተነሱት ካሃዲዎችና ጠባብ ብሔርተኞች ዘልዝለዉ ሊበሏት ከሚሯሯጡ ጠላቶችዋ ለመከላከል ሃይሉን ሳያጠናክር ፍጹም ዲሞክራሲን አመጣለሁ ብሎ ብቻዉን በመጋፈጡ ድርጅቱም ሆነ የሕዝቡ የነጻነት ጎሕ ተራዝሞ፣ ሕዝቡ የፋሽሽቱ ዱላ ስላስመረረዉ ከደርግ የባሰ ጨካኝ ገዥ አይመጣም ብሎ እጅና እግሮቹን አጣምሮ የቀንደኛዉ ጠላቱ የወያኔ ምርኮኛ ለመሆን በቅቶ የሚወዳት አገሩ ሊያጣት በቀነ ቀጠሮ ላይ ነዉ ያለዉ። እርግጥ ነዉ ኢሕአፓ እንደ ወያኔ ቤተ መንግስት ዉስጥ ለመግባት አንዴ የየመን ዘር አለን፤ ሌላ ግዜ ሱዳንና እኛ የአንድ አያት ዘሮች ነን ወይንም ደግሞ ወላጆቻችን የራሳቸዉን ወገን ክደዉ ከእናንተ ጋር ተሰልፈዉ ስለ ሞቱብን የደም ዋጋችን እንዲሆንን ስልጣን ላይ እንድታወጡን ብለዉ እንደ ወያኔዎች የነጭ ጫማ እግር ያልሳሙ ማለቴ አይደለም። ኢሕአፓ ስሕተት አልተሰራም ብሎ አያዉቅም:: ከስሕተቱም ብዙ ነገር እንደተማረ በግልጽ ተናግሯል:: ፍጹም ኢትዮጵያዊነቱም ከአሁን በፊትም ሆነ አሁንም በተግባር እያሳዬ ይገኛል። አገራችን በማጥፋት ላይ ያለዉን ወያኔን ሳይፈሩ የኢሕአፓ ስም ሲጠራ የቆላ ንዳድ እንደነደፈዉ ሰዉ

**የሚንቀጠቀጡ ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች በርከት ብለዉ ሳይ ለምን እንዲሕ ሊሆን ቻለ ስል ነበር ነገር ግን አሁን ግልጽ እየሆነልኝ መጥቷል፦**

1ኛ/ለግል ጥቅሙ ሲል በኢትዮጵያ አገሩ ላይ ለድርድር የማይቀመጥ ሀቀኛ የሕብረ ብሄር ድርጅት በመሆኑና የሕዝብን መፈክር በግንባር ቀደምትነት አንግቦ እንደ ዘመኑ እስስት ፖለቲከኞች ሲል በየደቂቃዉና ሰከንዱ ቀለሙን የማይለዋዉጥ ለሀቅ የቆመ ሆኖ ስላገኙትና የኢትዮጵያን ሕዝብ ማንም አጭበርባሪና ጠመንጃ ነካሽ እንደፈለገዉ አድርጎ እንዳይበዘብዘዉ እድል ባለ መስጠቱ ዘራፊዎች በጠላትነት ፈርጀዉ ይሕ ነዉ የማይባል የጥላቻ ስም ያሸክሙታል።

2ኛ/ለዉድድር እድል ተገኝቶ ብንቀርብ ሕዝቡን የማሳመን ችሎታ ስላለዉ በቀላሉ አሸንፎ ኢትዮጵያን የመራ እንደሆነ በሰራነዉ ጥፋት ለፍርድ ሊያቀርበን ስለሚችልና የስልጣን መያዙ ምኞታችን ሕልም ሆኖ ስለሚቀር አሁኑን ማጥፋት? መንጻት ሳይማሩ መኪና መግዛት ይልኳል ።

3ኛ/ስልጣንና ዶላር የማይቀይረዉ፣ ለአላማዉ የፅና፣ ዕበላ ባይነት ባህሬ የማይታይበት፣ የሕዝብ ታማኝ ተላላኪ  በመሆኑ እዉነትን እንደ ቀዳሚ መፈክሩ አንግቦ በመነሳቱ።

4ኛ/የ"ስልጡን ታጋይነት" ባሕሬ ስለማይታይበት፣ በኢትዮጵያዊነት ጠንካራ አቋም ያለዉ በመሆኑ፣ ስልጡን ታግይ ገንዘብ ካገኘ ሀረርን ለሶማሌዎች፤ ቋራና መተማን ለሱዳኖች፤ ባድሜና አሰብን ለሻእብያ፤ እዉነተኛዉን ወርቅ ከኢትዮጵያ አሸሽቶ በምትኩ ድንጋዩን ወርቅ ነዉ ብሎ ሕዝብን የሚያሞኝ፤ ድጋፍ ያገኘ እየመሰለዉ ዝነኝነት ያተረፉትን ግለሰቦችና አርቲስቶች የመቶ ዶላር ገጽ እያሳየ የሚያታልል፤ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያዉያን የሚወደደዉ የተዋሕዶ ቤተ ክርስትያናችንን ከፋፍሎ እርስ በራሱ እንዲናቆር የሚያደርግ ሁሉ ስልጡን ታግይ የሚል አዲስ ስም ሰጥተዉታል:: ኢሕአፓ ግን እንደዚህ ባለ  ልክስክስ ተግባር ባለመሰለፉ ከላይ የጠቀስኳቸዉ ነገሮች የሚያሟሉ በሙሉ በጠላትነት ፈርጀዉታል። በአገራችን አነጋገር ሽምብራ ቀረ----ቀለለ ማለት ነዉ። የሚስደንቀኝ ነገር ቢኖር የሆነ አዲስ ድርጅት እንደ ተቋቋመ በማግስቱ ስለ ተነሳበት አላማ ከማብራራቱ በፊት አፉን ለመፈታት እንደሚከላተፍ ሕፃን ልጅ እየተንገዳገዱ ኢሕአፓን ሲኮንኑ ለምን ተብለዉ ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ ከአሁን በፊት ብዙ ድርጅቶች ወድያዉኑ ተደራጅተዉ ሊፈርሱ የቻሉት የኢሕአፓ አፍራሽ እጅ ስላለበት ነዉ የሚል ማስጠንቀቅያ ስለተነገረን ወደ እኛም እንዳይዘምትብን ብለን ስለሰጋን ነዉ እንጅ ያደረገን ነገር የለም። ለተነሳበት አላማና ለሕልዉናዉ መጋፈጥ ያልቻለ እንዴት የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ ማዉጣት ይችላል::

ስለዚህ እርባታ የማያመጣ ተልካሻ ሁሉ ብዙ ነገር ሳያበላሽ መወገዱ ከፊታችን ተደቅኖ ለሚጠብቀን ትግል መቀነስ አንድ ይሆናል። ከምኖርበት አሜሪካ ዉስጥ አንድ ተመሳሳይ ነገር የገጠመኝን ላካፍላችሁ፡-አንድ ልጅ ትግል ምን እንደሚመስል አይቶና ሰምቶ የማያዉቅ ሁል ግዜ ስንገናኝ በጭፍንነት ስለ ኢሕአፓ ደካማ ጎን የሰማሁት እያለ በነጋ ጠባ ይጠይቀኛል:: በተቻለኝ አስረዳዋለሁ:: በይበልጥም ፕሮግራሙን አንብቦ እንዲረዳ አበረታታዉ አለሁ:: ይሕን ሁሉ ካደረኩ አስተሳሰቡ ለዉጥ ሊያመጣ ይችላል የሚል እምነት ስላደረብኝ ብዙ ሞከርኩኝ:: ስለድርጅቱ ምንም አይነት እዉቀት ሳይኖርህ ኢሕአፓን የሚጠሉ ባናፈሱት የስም ማጥፋት ዘመቻ ተበክለህ ጥላቻ ማሳደር አይገባህም ብዬ መክሬ በእኔና አንተ መካከል ሊኖረን የሚችለዉ ግንኙነት በአገር ልጅነታችን እንረዳዳ እንጠያየቅ ተባብለን ተስማምተን ተለያየን። ከአራትና አምስት ወር በኋላ ስልክ ደዉሎ ምናለ ነገ ምሳ አብረን ብንበላ ይለኛል:: እኔም እሺ ብዬዉ ቦታ ተቃጥረን በቀጠሮዉ ሰአት ተገናኝተን ምሳ በልተን እንደጨረስን የሰማውን ሊነግረኝ ከራሱ ጋር አገባ እሰጥ እያለ እንደ ሰባ በግ ብዙ ሲተነፍስ አየሁትና ባልሳሳት ልትነግረኝ ያቀድከዉ ያለ መሰለኝ ብዬ ጥርጣሬየን ስገልጽለት ሳያመናታ አዎ ይለኛል:: ቀጥል ስለዉ በዚህ ሳምንት አንድ ዜና ሰማሁኝ እዉነትነቱ ካንተ የበለጠ የሚያዉቅ ይኖራል ብየ ስለማላስብ እንድታብራራልኝ ብየ ነዉ ሲለኝ የማዉቀዉ ከሆነ ችግር የለም ስለዉ፡-በዚህ ሳምንት ኢሕአፓዎች አመታዊ ኮንፈረሳቸዉ ላይ ባለመስማማታቸዉ እንደ ሌሎች ድርጅቶች ስንጥቅጥቃቸዉ ወጣ ተባለ በጣም የሚያሳዝን ነዉ ሲለኝ: ከልብህ አዝነህ ነዉ ወይንስ ተደስተህ ስለዉ: አዬ ከልቤ ስላዘንኩኝ ነዉ ሲለኝ በል አትዘን ኢሕአፓ ቢገፈትሩት በቀላሉ ሊወድቅ የሚችል በሰምበሌጥ ግድግዳ መሰረት አልተገነባም ከሲሚንቶና ከብረት የተገነባ ስለሆነ ሃይለኛ ነኝ የሚል ሁሉ ሞክሮ አልተሳካለትም ነገር ግን አንዳንድ ትግሉ የረዘመባቸዉ ግለሰቦች በዉስጡ ተሰግስገዉ እንደ ካንሰር በሽታ ሲያምሱት የነበሩ በመሄዳቸዉ እሰይ የሚያሰኝ እንጅ የሚያሳዝን አይሆንም አንተ ስለማታዉቅ ነዉ እንጅ ከዚሕ የበለጡ ብዙ ደባዎች ተቋቁሞ ያከሸፈ ጠንካራ ድርጅት ነዉ ብዬ አሰናበትኩት:: ከዚህ ግለሰብ አስተሳሰብ የገባኝ ነገር ቢኖር የኢሕአፓ ጠላቶች ትንሽ ደካማ ጎን እንደሰሙ ያችን ለመተንፈስ ሳይተኙ እንደባነኑ ያድራሉ:: ያ ሁሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲል ያፈሰሰዉ ደም ዉሎ አድሮ የነፃነት ጮራ የፈነደቀ እለት ታሪክ ያስታዉሰዋል። ኢሕአፓ እስከዛሬ ድረስ ባለመጥፋቱ የራስ ምታት የሆነባቸዉ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች መኖራቸዉ ያለምክንያት አይደለም:: እንዲህ የሚያርበተብታቸዉ በሺ ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን ያለርህራሄ ጭካኔ በተሞላበት ፋሽሽቶቹ የደርግና ወያኔ አገዛዝ ሥር ትልቅ የመግደልና የማስገደል ሚና ተዋናኝ አክተሮች ስለነበሩ ከደሙ ንጹህ መስለዉ ለመታየትና ለማረሳሳት የሚነዙት ዉዥንብር የሚቀበላቸዉ ማንም ኢትዮጵያዊ የለም። ከኢሕአፓ ጋር ተሰልፈዉ አቋርጠዉ የፈረጠጡት ደግሞ ከደርግ ግድያ ለማምለጥና መገልበጫቸዉን ለማመቻቸት ነበር:: የቅርቡ ትዝብት

ደግሞ ከሰላሳ አምስት አመት ትግል በኋላ ክደዉ የፈረጠጡት ግለሰቦች ለታሪክ ያልታደሉ ጨለምተኞች ናቸዉ። ኢሕአፓ ከተለያዩ የፍራፍሬ አትክልቶች ተጨምቆ የወጣ እንጅ እንደ ወያኔ የአንድ ፍሬ ቅርንጫፍ ወጥ አይደለም። እኛ ኢትዮጵያዉያን ማወቅና ማስወገድ የሚገባን ቅድሚያ ነገር ቢኖር በሰራነዉ ጥፋት ተፀፅተን ለፈጸምነዉ በደል ይቅርታ ይደረግልኝ(ን)ብለን ከድርጊቱ ነፃ እንደመሆን ፈንታ በትእቢት ተወጥረን ሽፋፍነን ሰንካላ ምክንያቶች በመደርደር አታለን ማለፍ እንደ ትልቅ ጀብድ እንቆጥረዋለን፣ የፍርድ ቤቱ የአሰራሩ ጉዳይም ጀርባዬን እከክልኝ ያንተም እንዲታከክልህ እየተባባልን አገራችን ለዘመናት ገንዘብ ያለዉ ሲስቅ፡ የለለዉ እስር ቤት ሲማቅቅ የፍርደ ገምድሎች መነሃርያ ሆና ቆይታለች። ከእንደዚሁ አይነት አዙሪት መላቀቅ የምንችለዉ ዉሸትን እንደ መተዳደርያ ደንባችን ቆጥረን ሳይሆን እዉነትን ተቀብሎ ለሁሉም በእኩልነት የሚያስተናግድ በህዝብ ባለሞያዎች ረቆ ሁሉ የተስማማበት ማንም እንዳሻዉ ሊለዉጠዉ የማይችል ሕገ መንግስት ሲፀድቅ ብቻ ነዉ:: በአካባብያችን ሰላምና ፍቅር ሊኖር የሚችለዉ ያኔ ነው:: ያለበለዝያ ድክማችን ዉሃ ቢወቅጡት እምቦጭ ነዉ የሚሆነዉ:: ይህ ለረጅም አመታት ብዙ የሰዉ ልጅ ሕይወት የተከፈለበት ረጅም ትግል ነዉና። ኢሕአፓ ያለ ምክንያት አይደለም እናቸንፋለን የሚለዉን መፈክር ደግሞ ደጋግሞ የሚያስደምጠዉ:: ከሕዝብ ጎን የተሰለፈ የማታ ማታ በአሸናፊነት መዉጣቱ አይቀሬ በመሆኑ ነዉ። ኢትዮጵያ ማሪኝ ላላት መሃሪ ለመሆኗ ከጣልያን ጋር ሆነዉ ለሆዳቸዉ ብለዉ ተሰልፈዉ የወኀት ምህረት አግኝተዉ የአገሪቱን አንጡራ ሀብት ተቆጣጥረዉ እንደተንደላቀቁት አሁን ደግሞ እነ አቶ ስዬ አብርሃና ገብሩ አስራት ጦርነት መስራት የሚችሉት መድረክ ላይ ወጥተዉ ወያኔ ያለበሳቸዉ ካባ ሳይለዉጡ አዲስ የለዉጥ ሃዋርያዎች ነን እያሉ ያአዞ እንባ እየረጩብን ነዉ። እንተባበር ማለቱ ባልከፋ ነበር:: ነገር ግን የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም ሆነና ነገሩ የስንቱን ወላጅ አንጀት ያሳረሩባቸዉ ጣቶቻቸዉ ደም ሳይጠርጉ መልሰዉ እናሞኛችሁ ብለዉ መነሳታቸዉ የሚያሳዬዉ ሕዝብን ምን ያህል እንደናቁት ነዉ:: ሊያድኑት እንደ ቅዱስ ጌወርጊስ ፈረስና ጋሻ ጦር ይዘዉ አልደረሱለትም:: አቶ ስዬ በእዉነቱ ወደ ሕሌናዎ ለመመለስ ፈልገዉ ከሆነ መጀመርያ መደረግ የሚኖርባቸዉ ቅድመ ዝግጅት ማሟላት ይገባዎታል:: እኔ በርስዎ ቀጥታ ትእዛዝ ወንጀል ከተፈፀመባቸዉ ቤተሰዎች አንዱ ነኝ:: ታስረዉ እያሉም ባለፈዉ የሰሩት በደል ወደ ጎን ትቸ ከገቡበት እስር ቤት እንዲወጡ በፀሎት አስብዎት ነበር:: በመፈታቶምም እሰዬዉ ብያለሁ:: ለምን ቢሉኝ ፍርድ ሰጬም ሆነ ፍርድ ተቀባዩ የአረመኔዉ የወያኔ ልጆች በመሆናችሁ ነዉ። እንግዲህ እኔና አርስዎ የምንታረቀዉና አብረን ልንኖር የምንችለዉ ሃቀኛ የህዝብ ፍርድ ችሎት ላይ አብረን ቁመን ጥፋተኛ አለመሆንዎ ሲያረጋግጡልኝ ወይንም ችሎት ከመቅረባችን በፊት በመድረክ ላይ ወጥተዉ በእኔ ላይ ቅሬታ ያደረብህ ኢትዮጵያዊ ወገኔ ሆይ በማወቅ ወይንም ባለማወቅ ላደረኩት ጥፋት ይቅርታ እጠይቃለሁ ብለዉ በእናንተ ተይዘዉ ደበዛቸዉ የጠፉ እዉነተኛ ኢትዮጵያዉያን የታሰሩበት ቦታና ሞተዉ

ከሆነም  አሉ የሉም እያሉ ለ17 አመት እንቅልፍ ላጡት ወላጆችና ቤተሰቦች ቁርጡን ነግረዉ ቢያሳርፉቸዉ እኔም ሆንኩኝ ግፍ የተፈጸመባቸዉ በሞላ ቂማችን ፍቀን የመድረክ ባለደረቦችዎ እንሆናለን:: ይህን ለማድረግ ሀሞቱና ድፍረቱ ይስጥዎት:: ከላይ የገላጽኳቸዉን የማያሟሉ ከሆነ ግን እርስዎና መለስ በፉክክር የቀደዳችሁት ጨርቅ ለግባችሁ ያልጨረሳችሁት የጥፋት ጎዳና ቀጥሉበት::  ህዝቡ ለፍርድ እስከ ሚያቀርባችሁ ድረስ። ኢትዮጵያዉያን መሪዎቻችን ከሚያደርሱብን በደልና እሮሮ የተነሳ ሴጣኑ መለሰ ዜናዊ ነገ መልኩን ለዉጦ ነፃ ላወጣችሁ ቢለን አጨብጭበን የምንቀበለዉ ይመስላል:: አዲስ ድርጅት ተቋቋመ በተባለ ቁጥር በስተጀርባዉ ያዘለዉ መልእክት ሳንመረምር  አምነነዉ ገንዘብ ማዋጣት እንጀምራለን:: እንደዚህ እየሆነ ስንቱ ቀልዶብናል:: ስለዚህ ለእንደነዚሁ አይነቶች በቃ ብለን አብሮን አስከ ድል ቀን ከሚሞት ጋር ተሰልፈን የጀግና ሞት እንሙት ነዉ የምለዉ።  ወያኔዎች የግዛት እድሜያቸዉ ለማራዘም ቅድሚያ ማጥፋት የሚፈልጉት በኢትዮጵያዊነት ጠንካራ ፍቅር ያላቸዉ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ነዉ:: ለዚሁም እንደ ማስረጃነት የምጠቀመዉ ወያኔ በረሃ በትግል እያለ ደርግን ከመደምሰስ ይልቅ ኢሕአፓን ሲያሳድድና ሲገድል የነበረዉ፣ የምትሰሩት ድርጊት ለእናንተም ሆነ ለአገራችን አይበጃትም ብለዉ ለመካሯቸዉ ሁሉ ሰበብ እየፈለጉና ከተኙበት አፍነዉ በመዉሰድ ደበዛቸዉን ማጥፋት፣ በጅምላ በመግደል፣ የዉሸት ክስ መሥርተዉ ከሳሽና ፍርድ ሰጮች በመሆን ስንቱን የዋህ ሕዝብ ያለፍርድ እስር ቤት በመወርወር ረግጠዉ መግዛቱ ሊሳካላቸዉ ባለመቻሉ አሁን ደግሞ የሃይማኖት ጠበብቶች ነን እያሉ የዉሸት መስቀል ያላቅማቸዉ ተሸክመዉ ይሄዉና እዉነተኛ አማኙን ሕዝብ እርስ በራሱ ያለ ርህራሄ እንዲፋጅ ከመንገድ ዳር ቆመዉ አንዱ ሲቸነፍ ሌላዉን በመርዳት የስንቱ ህዝብ ደም ያለምክንያት እንዲጎርፍ መጠን የለለዉ ግፍና በደል በህዝቡ ላይ እየፈፀሙ ነዉ። የወያኔ መሪዎች ከህዝቡ በዘረፉት ገንዘብ በተነሳ በመካከላችዉ ልዩነት በመነሳቱ በሙስና እየተወነጃጀሉ እስር ቤት ተወራዉረዋል::

ሲፈቱም ያለፈዉን በደላቸዉ ሸፋፍነዉ ለማለፍ አዲስ የመደበቂያ ቦታ አግኝተዋል:: ይህ ቦታም ጥንት የበረሃ ስሙ ደደቢት ዋሻ ሲሆን አሁን የከተማ አዲሱ መጠርያዉ ደግሞ የሃይማኖት ዋሻ ነዉ የሚባለዉ። ይሕ የከተማ ዋሻ የነብሰ ገዳይ መደበቂያ መሆኑ የተረዳሁት ታምራት ላይኔ የተባለ ቀንደኛ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት መለሰ ዜናዊ እድሜና ጤና ይስጥልኝ መጀመርያ ለጠቅላይ ምንስቴርንት ማዕረግ አበቃኝ አሁን ደግሞ በእርሱ ትእዛዝ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስን ለማግኘት ችየ አለሁ ለዚህ ደረጃ ያበቃኝ ጌታዬ ክፉ አይንካብኝ እያለ የአባይን ፏፏቴ የሚያስንቅ እምባ በሂደበት መደበቂያ ቦታ እያፈሰሰ የወያኔ ወንጌላዊ መፅሃፍ ተሸክሞ ለሁለተኛ ዙር የኢትዮጵያን ህዝብ ሊበድል መሯሯጥ በሰፊዉ ተያይዞታል። ጎበዝ ነቃ እንበል እንጅ! የዋህነት እኮ በሁለት ሊተረጎም ይችላል:: ትላንት ትእዛዝ እየሰጡ በወንድም እህቶቻችንና በምንወዳት አገራችን የሞት ፍርድ የበየኑብን ዳግም እናሞኛችሁ እያሉ ሲያለቅሱ

አብረን ማልቀስ ይኖርብናል? ዉድ አገር ወዳድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! አሁን ደርሰንበት ያለዉ ዘመን ለተንኮለኞችና ዉሸታሞች የምንበረከክበትና የምናጨበጭብበት እየሆነ ነዉ ያለዉ:: እነዚህን አጸያፊ ቡዱኖች ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ቀርፈን መጣል የምንችለዉ በአንድነት ተባብረን ስንነሳ: ለህዝብ የቆመዉን ወገን ለይተን ስናዉቅ ብቻ ነዉ: ከፊታችን ተደንቅሮ ያለዉን ነቀርሳ ጠላታችን ማጥፋት የምንችለዉ:: ነገር ግን የወያኔን የገደል ማሚቶ ጭሆት እየሰማን መልሰን የምናስተጋባ ከሆን መፍትሄዉን ሳይሆን የምንሻ የጥፋቱም ተባባሪዎች ሆነን በታሪክ ልክ እንደ ወያኔዎች የምንጠየቅ መሆናችን እንድንረዳዉ አሁኑን ሚናችን መለየት ይኖርብናል: ኢትዮጵያ አገራችን ሕልዉናዋን ለማረጋገጥ:: እርስዋ ከለለች ለስልጣን መራቆቱ የት ሆኖ ለመግዛት ነዉ።

ኢትዮጵያ አገራችን ለዘልአለም ትኑር!